# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 173 ጳጉሜ 3 2003 ገጽ 1

**እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2005 እስከ 2010 ባሉት ዓመታት ውስጥ የአሜሪካ የዲፕሎማቲክ ሚስዮኖች ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የላኳቸው መልዕክቶች ከአሜሪካ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ቡድን እጅ ውስጥ ገብተው ሰሞኑን "ዊኪሊክስ" በተሰኘ ዓለም ዓቀፍ የመረጃ ድረገጽ ላይ ተዘርግፈዋል።**

**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህም መረጃዎች ሥርዓት ባለው መንገድ መመርመር ጠቃሚ ትምህርቶችን ይሰጣል፤ ለትግላችንም አስተዋጽኦ ይኖረው ይሆናል ብሎ ያምናል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዊኪ ሊክስ እጅግ በርካታ የሚስጥራዊ መረጃ ኗጦችን ዘረገፈ፣ የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ ከአራት ሺህ በላይ የሚሆኑ ሚስጥራዊ መረጃዎች ተጋለጡበት

«የሚስጥራዊ መረጃዎች ተራራ» በሚል የአልጃዚራ የዜና አውታር የገለጸውና የአሜሪካ ዲፕሎማቲክ ሚስዮኖች በሚስጥር የሚለዋወጡአቸውን መልእክቶች ማጋለጥ የጀመረው ዊኪሊክስ ባለፈው ሳምንት እጅግ በርካታ የሆኑ መረጃዎችን በመረጃ ድረ ገጹ ላይ የለቀቀ ሲሆን፣ የዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ከዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜርካ ጋር የተለዋወጣቸውን ሚስጥራዊ መልእክቶችና፣ አንዳንድ በዘረኛው አገዛዝ የስልጣን ወምበር ላይ የተቀመጡ ባለስልጣናት አገዛዙን ያጋለጡባቸው ከአራት ሺህ አምስት መቶ በላይ አስገራሚ ሚስጥራዊ መረጃዎች ይፋ ሆነዋል።

ዊኪሊክስ ለአለም ህዝብ ይፋ ያደረገው ግዙፍ የመረጃ ተራራ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር እስከ 2010 በነበሩ ጊዜያቶች በአለም ዙሪያ የተሰማሩ የአሜሪካ ዲፕሎማቶች የየተሰማሩባቸውን አገሮች ጉዳይ አስመልክቶ ለአገራቸው መንግሥት ያስተላለፉት እንደሆነ ሲታወቅ መረጃው ሊወጣ የቻለው፣ ከአሜሪካኖች ቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ አፈትልኮ በዊኪልክስ ቡድን እጅ በመግባቱ እንደሆነ ቀደም ብሎ መገለጹ ይታወሳል።

ዊኪሊክስ ይፍ ባደረጋቸው በዚህ መረጃ ውስጥ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የወያኔ አገዛዝ የሚያከናውናቸው አበይት ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ክንዉኖች ምን እንደሚመስሉና በዚህም ላይ የአሜሪካ መንግሥት እይታ ምን እንደሆነ የሚገለጹ ከአራት ሺህ በላይ ሰነዶች ተዘርዝረዋል። በዚህም መሠረት አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ. ወያኔ አገራችንን በምን አይነት ሁኔታ እየገዛ እንዳለ፤ በወያኔ ሹመኞች መካከል የአገዛዝ ቀንበራቸውን በፈረጠመ ጡንቻ ለማራዘም እየባዘኑ እንዳለ፤ የምዕራቡን የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት እነመለስ ዜናዊ ለውጪው አለም በሚለፍፉት ዲሞክራሲያዊነትና በተግባር መካከል ስላለው ክፍተትና በአገሪቱ ውስጥ እየተካሄደ ስላለው አፈናና ወዘተ በሠፊው የሚያትቱ መረጃዎች ለህዝብ ዕይታ ቀርበዋል።

ዊኪሊክስ የለቀቃቸው መረጃዎች በኢትዮጵያዊያን የነጻነት ትግል ላይ ሊኖረው የሚችለው አንድምታ ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲያብራሩልን የግንቦት ሰባት ንቅናቄን ከፍተኛ አመራር አካል በስልክ አነጋግረን በሰጡን ምላሽ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍርድቤት የሱዳኑን ፕሬዝዳንት አልባሺርን ለማሳሰር ያወጣው የዕሥር ትዕዛዝ መለስ ዜናዊ "ነግ በኔ" እንዲል አድርጎታል ሲል በዊኪሊክ ላይ ሾልኮ የወጣው የአሜሪካ የምስጢር ሠነድ አጋለጠ

የሱዳኑ ፕሬዝዳንት አልባሽር ከሥልጣን ይወገዱ ዘንድ መለስ ዜናዊ ፍላጎት እንዳለው ለአሜሪካ ባለሥልጣናት መናገሩን ይፋ አድርጎ የነበረው የአሜሪካ ኤምባሲ መረጃ፤ አልበሽር ዳርፉር ውስጥ ለተፈጸመው የዘር ማጥፋት በአለም አቀፍ ፍርድቤት እንዲከሰሱ መደረጉ አስደንግጦታል ማለቱን ዊኪሊክስ ይፋ ያደረገው መረጃ አጋለጠ።

ዊኪሊክስ ይፋ እንደ አደረገው የአሜሪካ ምስጢር መረጃ፤ የአለም አቀፉ ፍርድቤት አልባሽር ላይ የመሰረተው ክስ በሱዳን ውስጥ አለመረጋጋትን ከመፍጠር አልፎ ወደ ኢትዮጵያ በመዝለቅ የጸጥታ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ብሎ መለስ ዜናዊ እንደሚሰጋና በተለያዩ አጋጣሚዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጸሙት ጭፍጨፋዎችና በተለይም በኦጋዴን ክልል ለደረሰው የዘር ፍጂት ወንጀል በሃላፊነት ያስጠይቀኛል የሚል ፍርሃት እንደለቀቀበት አረጋግጦአል።

መለስ ዜናዊ በአንድ በኩል በሱዳን ውስጥ የአስተዳደር ለውጥ እንዲኖር የአልበሽር መንግሥት ላይ መዘመት አለበት በማለት አመሪካኖችን እንደሚያግባባ ያጋለጠው መረጃ ፤ በጋምቤላ፤ በኦጋዴንና በድህረ ምርጫ 97 በአገራችን የተለያዩ ቦታዎች የተፈጸመው ጭፍጨፋ ዳርፉር ውስጥ ከደረሰው ሰቆቃ ጋር አቻነት እንዳለው በዚህም ምክንያት የአልበሽር ለአለም አቀፍ ፍርድቤት መቅረብ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ለመለስ ዜናዊም እንደማይቀርለት ማሳየቱን የአሜሪካ ባለሥልጣናት እንደሚያምኑበት ግንዛቤ መፍጠሩን ለማረጋገጥ ተችሎአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ህዝባችንን በጠነከረ የብረት አለንጋ እየገረፈ ለመግዛት ካለው ፍላጎት የተነሳ ለአለም አቀፍ ፍርድቤቱ እስከዛሬ ምንም እውቅና እንዳልሰጠና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአፍርካ ህብረት አማካይነት የፍርድቤቱን ውሳኔ የማጣጣል ዘመቻ እንዲከፍት አድርጎታል።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የዘረኛው አገዛዝ በትር፡ ታማኝ አገልጋዮቹንም እየገረፈ ነው፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ምክትል ፕሬዚዳንት ከኃላፊነቱ መነሳቱ ታወቀ

በኢትዮጵያዊያን ትከሻ ላይ እንደመዥገር ተጣብቆ የሚገኘው የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት በስልጣናቸው ላይ ስጋት የሚፈጥርባቸውን ማናቸውንም ሃይል ከማጥፋት ወደሁአላ እንደማይሉ በተደጋጋሚ ያሳዩና ያስመሰከሩ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን የቤሻንጉል ጉምዝ ክልል ምክትል ፕሬዘዳንትና የወያኔ አገልጋይ የነበረው ሰብስቤ ንሳጼ ጋስ በግምገማ ሰበብ ከስልጣን መወገዱን ምንጮችን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የቤሻንጉል ጉምዝ ክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወያኔያዊ ግምገማን ካካሄደ በሁአላ ሰብስቤን ከነሐሴ 29 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ያደረገ መሆኑ ታውቁአል። በክልሉ ለወያኔው ዘረኛ አገዛዝ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ባለስልጣናት የማባረር ተግባር በዚሁ ሳያቆም የክልሉ የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ታዬ ሀብቴ፣ የክልሉ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ባይሳ ቤሴ ወንበርንና የክልሉ የማይክሮ ፋይናንስ ሥራ አስኪያጅ ዘለዓለም መንገባ በኮዬ በዚሁ ግምገማ ከኃላፊነታቸው መነሳታቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል፡፡

ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ የቆየው ሰብስቤ ንሳጼ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ቤጉሕዴፓ) ምክትል ሊቀመንበር መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ቀደም ባሉት ዓመታትም የክልሉ የውኃ ሀብት ቢሮ ኃላፊ፣ የክልሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚና በሌሎችም ኃላፊነቶች ላይ መሥራቱን ምንጮቹ ለዘጋቢያችን ገልጸዋል፡፡ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛው አገዛዝ ታማኝና አገልጋዮች ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ጥቂት የህብረተሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚዉን በበላይነት እንዲቆጣጠሩ የማድረግ ተግባሩን ቀጠጥሏል፣ ስኩዋርን የማከፋፈል ድርሻ የምርጦቹ እንዲሆን ተወሰነ

ቀደም ብሎ በሃገር ውስጥ ስኳርን በጨረታ በመሸመት ለቸርቻሪ ነጋዴዎች በጨረታ የማከናወኑ አሰራር እንዲቀርና ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት (ጅንአድ) ፣ለሚመርጣቸው ነጋዴዎችና ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ብቻ እንዲሰጥ መወሰኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ፡፡

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ቀደም ብሎ ስኳር ለገበያ ተጠቃሚዎችና ሸማቾች የሚቀርብበትን የጨረታ አሠራር በመሰረዝ፣ አዲስና ምርጦችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር እንዲሰፍንም የተደረገው ነጋዴዎች ለራሳቸው ጥቅም ብቻ በማሰብ የስኳር ገበያውን እየረበሹና እጥረት እየፈጠሩ መጥተዋል በሚል ሰበብ መሆኑ ታውቁአል፡፡

ቀደም ብሎ ስኩዋርን በጨረታ ከማከፋፈያ በመግዛት ለቸርቻሪ ነጋዴዎች የማከፋፈል ስራን ሲያከናውኑ የቆዩ ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ ነጋዴን ዘጋቢያችን አነጋግሮ በሰጡት አስተያየት ስኩዋር እንደስሙ ሁሉ ስኩዋር እየሆነ ከመጣ ዘመን አልፎታል፣ ከፍተኛ የሆነ ትርፍ የሚግበሰበስበት የምግብ ፍጆታ ነው። የወያኔ አገዛዝ እንዲህ አይነት የፍጆታ እቃዎችንም ሆነ ሌሎች ከፍተኛ የሆነ ገቢ የሚያስገኙ ተቋዋማትን በምንም መልኩ ከእጁ እንዲወጡ አይፈልግም፣ ከዚህም በተጨማሪ ከአንድ ክልል ለመጡ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትና ለወያኔ ደጋፊዎች የተለየ አገልግሎትና ጥቅምን በመስጠት እንደስኩዋር ያሉ ከፍተኛ ገቢንና ትርፍን የሚያመጡ ሸቀጦች ለነኝህ ግለሰቦች እንዲሰጥ የማድረግ ተግባር ከጀመረ ቆይቱአል። ወያኔ ደረጃ በደረጃ ጫካ ውስጥ ሲያልም የነበረውን የበላይነት እቅዱን ቀስ በቀስ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ልብ እያልን ነው። ባሁኑ ሰአት ከፍተኛ የሚባሉ የንግድ ተቋአማት ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ ሁላችንም እናውቃለን፣ ብለዋል። በመጨረሻም የንግዱ ማህበረሰብ አባላት የሆንን ሁሉ ይህንን በጥንቃቄ መገንዘብ ሳይረፍድብን ከወያኔ ጋር የመጋፈጫ ጊዚያችን አሁን ነው፣ አለዚያ ፍጹም ልናገግም ወደማንችልበት አዘቅት ውስጥ ስንገባ ይታየኛል በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በጅምላ ማሰሩን ቀጠሉአል፤ ሰሞኑን በሽብርተኝነት ሥም 29 የኦሮሞ ተወላጆች በቁጥጥር ሥር መዋላቸው ተገለጸ

ህዝባዊ ተቃውሞ ሊቀሰቀስብኝ ይችላል በማለት እንቅልፍ እያጣ የመጣው የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን በዜጎች ላይ ጅምላ እስራት ማካሄዱን በመቀጠል የኦነግን የሽብር ዓላማ ያራምዳሉ በማለት 29 ሰዎች ማሰሩን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የዘረኛው ወያኔ ሰለባ ከሆኑት 29 ግለሰቦች መካከል የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግሬስ (ኦሕኮ)ና የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) ፓርቲዎች አባል የሆኑ ዘጠኝ ግለሰቦች ይገኙበታል።

ጥላሸት በመቀባትና ያልሰሩትን ወንጀል ሰርቻለሁ ብለው እንዲቀበሉ በማሰቃየት ተግባሩ የሚታወቀው ዘረኛዉ አገዛዝ የአሁኖቹን ታሳሪዎች "በኅቡዕ መዋቅሮች በመደራጀት ለሽብር ተግባር ተልዕኮ የሚውሉ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችንና ፈንጂዎችን በመያዝና ደብቆ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ሙከራ" የተያዙ ናቸው በማለት የተለመደ ፕሮፓጋንዳውን በመንዛት ላይ እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን መረጃ አመልክቱአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሾልከው ካመለጡ የአሜሪካ የዲፕሎማሲ ሰነዶች የምንማራቸው ሃቆች

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2005 እስከ 2010 ባሉት ዓመታት ውስጥ የአሜሪካ የዲፕሎማቲክ ሚስዮኖች ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የላኳቸው መልዕክቶች ከአሜሪካ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ቡድን እጅ ውስጥ ገብተው ሰሞኑን “ዊኪሊክስ” በተሰኘ ዓለም ዓቀፍ የመረጃ ድረገጽ ላይ ተዘርግፈዋል። በዚህም ምክንያት በከፍተኛ ምስጢርና ጥንቃቄ የተላኩ መረጃዎች ለአደባባይ እይታ በቅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የአሜሪካ ዲፕሎማቶች ወደ አሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ የተላኩ ከአራት ሺህ በላይ ሰነዶች ይገኛሉ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህም መረጃዎች ሥርዓት ባለው መንገድ መመርመር ጠቃሚ ትምህርቶችን ይሰጣል፤ ለትግላችንም አስተዋጽኦ ይኖረው ይሆናል ብሎ ያምናል።

ሰነዶቹ በጥንቃቄ ከተጠኑ:-

- በአምስቱ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ፓለቲካ በተመለከተ በአሜሪካ ዲፕሎማቶች አተያይ ላይ የመጣው ለውጥ፣
- ሰዎች ሲለዋወጡ በዲፕሎማሲው ላይ ያለው ተጽዕኖ፣
- አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የምትከተለው የፓሊሲ መሠረት ምንነት፣
- የመለስ ዜናዌ አገዛዝ በዲፕሎማቶቹ ዓይን ምን እንደሚመስል፣ እና በመሳሰሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በርካታ ዓይን ከፋች እውነታዎችን አንጥሮ ማውጣት ይቻላል ብሎ ግንቦት 7 ያምናል። ሆኖም መረጃዎችን ሙሉ በሙሉ ማንበብ፤ አንብቦም መረዳት እና ለትግላችን ያላቸውን እንድምታ መመዘን ጊዜ የሚፈጅ ጉዳይ ነው። ስለሆነም እስካሁን ከታዩ ሰነዶች የተገኙት አጠቃላይ ግንዛቤዎች የማስቀመጥ አስፈላጊና ወቅታዊነት ታምኖበታል።

በዚህም መሠረት አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ዋሽግተን ወደሚገኘው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ከላካቸው እና እስካሁን ከተዳሰሱት ሰነዶች አጠቃላይ ይዘት በመነሳት የሚከተሉትን ድምዳሜዎች ላይ መድረስ ይቻላል።

I. **ጥሬ ሃቆች**

1. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘረኝነት፤ “ሁሉንም ጠቅላይ” አምባገነንነቱ እየጨመረ የመጣ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት የሰላማዊው ፓለቲካ ሜዳ እየጠበበ መምጣቱን አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በደንብ ያውቃል፤ይህንኑም ዋሽንግተን ለሚገኘው የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አሳውቋል።
2. የመለስ ዜናዌ አገዛዝ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን - በእስረኞች ላይ አሰቃቂ ሰቆቃዎችን (ቶርቸር) የሚፈጽም መሆኑን ጭምር - አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በደንብ ያውቃል፤ ይህንኑም ዋሽንግተን ለሚገኘው የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አሳውቋል።
3. የመለስ አገዛዝ የሚደሰኩረው የኢኮኖሚ እድገት ውሸትነት፤ እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነትና ሊያስከትላቸው ስለሚችሉ ፓለቲካዊ ውጤቶች አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በደንብ ያውቃል፤ ይህንኑም ዋሽንግተን ለሚገኘው የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አሳውቋል።
4. ከመለስ ዜናዊ የቅርብ ባለሟሎች እንኳን ሳይቀር በሥርዓቱ የተማረሩ እና ተስፋ የቆረጡ መኖራቸው አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ መረጃ ደርሶታል፤ ይህንኑም ዋሽንግተን ለሚገኘው የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አሳውቋል።

II. **መራር እውነታ**

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን በአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ ፓሊሲ ላይ ይኸ ነው የሚባል ለውጥ አልታየም።

III. **እንድምታ**

ይህ ቢያንስ ሶስት መሠረታዊ ጉዳዮችን ያስጨብጠናል።

1. ፓለቲካ በንድፈሃሳብና በተግባር የቱን ያህል የተለያዩ እንደሆነ እናይበታለን።
2. በመለስ ዜናዊ አገዛዝ እየደረሰበን ያለውን ግፍና መከራ ለኃያላን አገራት ማሳወቅ ጠቃሚ ቢሆንም እንኳን ማወቃቸው ፓሊሲያቸውን ለማስቀየር በቂ ላይሆን እንደሚችል ያረጋግጥልናል። ይህ እንድምታ “መቼና ምን ሲሆን ነው ኃያላን አገሮች ከሌሎች አገራት ጋር ያላቸውን ፓሊሲ ለመመርመር ፈቃደኛ የሚሆኑት?” የሚለውን ጥያቄ በጽኑ እንድናስብበት ያደርገናል።
3. ኢትዮጵያን ችግር መፍታት ያለብን እኛው መሆናችን ያስገነዝበናል።
4. ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የምናደርገው ትግል የኃያላን አገራቱን ዲፕሎማቶችን ልቦና ቢማርክ እንኳን ተጨባጭ ድጋፍ የሚያደርጉበት ደረጃ ላይ አለመድረሳቸውን ሰነዶቹ ያረጋግጡልናል። ግንቦት 7 ከዚህ በፊትም ደጋግሞ እንደአስገነዘበው ሁሉ ለኢትዮጵያ መፍትሄ ማምጣት ያለብን እኛው ራሳችን ነን።

ድርጅታዊ ጥንካሬ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ ያረጋግጥናል።

ለተሳካ የዲፕሎማሲ ሥራም የጠንካራ ድርጅት መኖር ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ ከሰነዶቹ የምንረዳው እውነታ ነው። የኃያል ሃገሮች ተጨባጭ የዲፕሎማሲ ድጋፍ ለማግኘት ጠንክሮ መገኘት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሆነ መመዘኛ የመሆኑ ሃቅን ሰነዶቹ ይፈነጥቁልናል።

ስለሆነም ግንቦት 7 እንደትናትናው ሁሉ ዛሬም የዲፕሎማሲ ትግላችንን እናጠናክር፤ ሆኖም ግን የበለጠው ትኩረታችን ራሳችንን በማጠናከር ላይ ይዋል ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ሰዎችን ከኢትዮጵያ አባረረ

ከመቼውም ጊዜ በላይ በተለያዩ አስጨናቂ ህዝባዊ አጀንዳዎች ተወጥሮ የሚገኘው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን እንደቆሰለ ጅብ እያረገው ሲሆን የተለያዩ ሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በማጣራት ላይ ይገኙ የነበሩ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ሰዎችን በ 24 ሰአት ጊዜ ውስጥ ከሃገር ማባረሩን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

እንደወያኔ በሥልጣን ላይ ለአሥርተ አመታት የቆዩትን አምባገነን የሰሜን አፍሪካንንና የአረብ አገራት ገዥዎችን እያርበደበደ ያለው አይነት ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቀስ ይችላል በማለት በስጋትና ፍርሃት የተጠመደው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፤ ሰሞኑን በጀመረው አዲስ የእስር ዘመቻ የኦፌዲን ምክትል ሊቀ-መንበር የሆኑት አቶ በቀለ ገርባናንና የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ አመራር አባል አቶ ኦልባና ሌሊሳን ጨምሮ በርካታ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎችን በቁጥጥር ሥር ባደረገ በጥቂት ቀናት ውስጥ የአምንስቲ እንተርናሽናል ሰዎች ከአገራችን መባረር እየተፈጸመ ያለው መብት ጥሰት በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ እንዳይታወቅ ለመከላከል ካለው ፍላጎት የመነጨ እንደሆነ ተገምቶአል። ለዚህም እንደማስረጃ ሊቆጠር የሚችለው አቶ በቀለ ገርባና አቶ አልባና ሌሊሳ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ተንቀሳቅሰው ከነበሩት ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ልዑካን ቡድን ጋር ከተገናኙ በኋላ “የሽብርተኝነት ክስ ” በፈጠራ ተለጥፎባቸው እስር ቤት እንዲወርዱ መደረጋቸውን ኢሳት ታማኝ ምንጮቹን ጠቅሶ በመዘገቡ ነው።

እንደ ኢሳት ዘገባ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ሰዎች ለሥራ ጉዳይ አዲስ አበባ ውስጥ በቆዩባቸው ጊዜያቶች 24 ሰዓት ሙሉ በደህንነቶች ካሜራ ክትትል ስር የነበሩ ከመሆናቸውም ባሻገር፤ ከተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ጋር በመገናኘታቸው በ24 ሰዓት ውስጥ የኢትዮጵያን ድንበር ለቀው እንዲወጡ ከዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሰረት፤ ለ 12 ቀናት ሊያደርጉት የነበረውን ቆይታ አቋርጠው ለመመለስ መገደዳቸው ታውቁአል።

አቶ በቀለ እና አቶ ኦልባና የታሰሩት የአምነስቲ ሰዎች ከኢትዮጵያ መባረራቸውን ተከትሎ ሲሆን፤ ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ልዑካን ጋር ሲወያዩ ደህንነቶች ያነሷቸው ፎቶዎች፤ በሽብርተኝነት ለተመሰረተባቸው ክስ እንደ አንድ ማስረጃ መቅረቡም ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሰሞኑን ከጊንጭ ከተማ የተያዙት ሰባት የመድረክ አባላት ለምን እንደታሰሩ እስካሁን ያልተገለጸ ሲሆን ተመሳሳይ የሽብርተኝነት ታርጋ ይለጠፍባቸዋል የሚል ግምት እንዳላቸው፤ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል የሆኑት አቶ አንዷለም አራጌ ለኢሳት መናገራቸውን ኢሳት ዘግቡአል።

ኢሳት ረሀብ ከፉኛ በተከሰቱባቸው አካባቢዎች ምንም ዓይነት ፎቶግራፍ ማንሳት በኢትዮጵያው ዘረኛ አገዛዝ መከልከሉን የተባበሩት መንግስታት ሰሞኑን ባወጣው ሪፖርት ላይ መጠቆሙን አቶ አንዷለም መናገራቸውን ዘግቡአል። አቶ አንዷለምን በመጥቀስ እንደዘገበው፤ የመንግስታቱ ድርጅት ልዑካን ጥናታቸውን ሲጨርሱ ባወጡትና ለፓርቲያቸው በላኩላቸው ሪፖርት ላይ ፤በኢትዮጵያ የተከሰተውን ረሀብ ተከትሎ የተመድ ልዑካን ወደተለያዩ በረሀብ የተጠቁ አካባቢዎች ቅኝት ሲያደርጉ ምንም ዓይነት ፎቶ እንዳያነሱ መንግስት እገዳ እንደጣለባቸው ታውቁአል።

ቁጥራቸው ከ50 በላይ የሆኑ አባላቶቹ ያለአንዳች ማስረጃ መታሰራቸውን፣ ተከትሎ ፤የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን)፤ ቀደም ሲል በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች አባሎቹ መታሰራቸውን፣ መደብደባቸውንና ከሀገር እንዲሰደዱ መደረጋቸውን በማስታወስ፤ ዛሬም ይህ የገዢው ፓርቲ ፖለቲካዊ ሴራ ሊቆም አልቻለም ሲል ገለጹአል።

የኦፌዴን ም/ ሊቀመንበርና የውጭ ግንኙነት ሃላፊ እንዲሁም የመድረክ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ በቀለ ገርባ ለነፃነት በመታገላቸው ብቻ፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርነት ከሚያገለግሉበትና የዶክትሬት (የፒኤችዲ) ጥናታቸውን ከሚያከናውኑበት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አቃቂ ካምፓስ ተይዘውና ወደ አዳማ ተወስደው ቤታቸው ከተበረበረ በኋላ፤ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደርጎ በፌዴራል ማዕከላዊ ምርመራ ቢሮ መታሰራቸውን ዋና ፀሀፊው ገልጸዋል።

እንደ ዋና ጸሃፊው መግለጫ ”የወያኔ አገዛዝ አቶ በቀለን ለማሰር የተጠቀመበት ሴራ ዘወትር ኦሮሞ የሆነን ሰው ሲወነጅል እንደሚጠቀመው “ኦነግ “የሚል ካርድ በመምዘዝ ነው‘ ያሉ ሲሆን” አቶ በቀለ ገርባ የታሰሩት ኦነግ ስለሆኑ አይደለም፤ ይልቁንም የኦፌዴን ፓርቲ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ፤ የገዢውን ፓርቲ ኢፍትሃዊና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን፤ ሀገርና ዓለም በተጨባጭ እንዲያውቀው ተግተው በመሥራታቸውና በመድረክ ጥላ ሥር ለፓርቲዎች አንድነት አበክረው በመንቀሳቀሳቸው ነው‘ ብለዋል፡፡

ቀጥለውም “ገዢው ፓርቲ፤ አቶ በቀለን ያሰረው፤ ሌሎች ለመብታቸው የሚተጉ ዜጎችን ለማስፈራራት ነው፤ ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈራው ጽዋው እስኪ ሞላ ብቻ ነው። ህዝባችን ልክ እንደ ቱኒዚያ እና ግብፅ ሕዝብ ለነፃነቱ ይቆማል” ብለዋል።

ቀደም ብሎ የቢቢሲ ጋዜጠኞች ወደ ኢትዮጵያ ቱሪስት መስለው በመግባት ስላጠናቀሩት ዘገባ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በተደጋጋሚ ሲያስተባብልና፤ የቢቢሲ ጋዜጠኞች ዘገባውን ሚዛናዊ ለማድረግ የአካባቢዎቹን መስተዳድሮች አስተያዬት ማካተት ነበረባቸው የሚል ኡ ኡ ታ ሲያሰማ የቆየ ሲሆን ይህን ኡ ኡ ታ ተከትሎ የኢትዮጵያን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በቅርበት የሚከታተሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለግንቦት ሰባት ዘጋቢ በሰጡት አስተያየት የቢቢሲ ጋዜጠኞች የዘረኛውን አገዛዝ ባህሪ ጠንቅቀው በማወቃቸው ዘገባቸውን በተገቢው መንገድ ለማጠናቀር የተጠቀሙት ስልት የሚያስመሰግናቸውና እሰየው የሚያሰኝ ነው ብለዋል።

# ኢትዮጵያ ሶማሊያን አትሆንም !!!

*ከዝግጅት ክፍላችን*

ከሰሞኑ በህወሃት መንደር ስንሰማው የኖርነው ሟርት እንደገና ታድሶ መወራት ጀምሯል። ሊቢያ፤ ግብጽ፤ ቱኒዚያና ሌሎችም አገሮች ውስጥ የሚታየው ዓይነት አብዮት በኢትዮጵያ ቢነሳ ኢትዮጵያ ትጠፋለች የሚል የተለመደ ሟርት በሰፊው መወራት ጀምሯል። ይህ ባዶ ማስፈራሪያ አይደለም። ህወሃቶች ህዝቡ በነጻነት ከሚኖር ይልቅ ዜጎች እርስ በርሳቸው ተጫርሰው አገሪቷ ብትጠፋ ቅር የሚላቸው ግለስቦች እንዳልሆኑ የ1997 ዓ.ም ምርጫና ውጤቱ በቂ ምስክር ነው።

ኢትዮጵያ በብዙ ብሄሮችና ሃይማኖቶች የተከፋፈለች ነች። ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ አንዳች ዓይነት የለውጥ ፍላጎት ቢነሳ እልቂትና መበታተን ይከተላል እያለ መለስ ዜናዊ ማላዘን ይዟል።

እንዲህ ዓይነቱን ሟርት የግብጹ ሆሲኒ ሙባረክ፤ የቱኒዚያው ቤኒ ዓሊ፤የሊቢያው ሙሃመድ ጋዳፊ እና ሌሎችም ዘራፊ አምባገነኖች አሟርተውታል። ህዝቦች በአንድነት ለነጻነታቸውና ለክብራቸው ፀንተው ቁመው ሟርተኞችን አሳፍረዋቸዋል። የእኩልነት፤ የነጻነትና የፍትህ ጥያቄ ሰው የመሆን ጥያቄ እንጂ የዚህና የዚያ ብሄረሰብ ወይም ደግሞ የዚህና የዚያ ሃይማኖት ጥያቄ ብቻ አይደለም። ምንም እንኳን መለስና ግብረአበሮቹ ጆሮ እያላቸው የማይሰሙ ዓይን እያላቸው የማያዩ ፍጡራን በመሆናቸው የሚነገራቸውን ሊያደምጡ ባይችሉም ደግመን ደጋግመን ኢትዮጵያችን እንደ ሶማሌ እንደማትሆን አበክረን መንገር እንፈልጋለን። የኦትዮጵያን ጥያዌ አንድ ነው። የነጻነት፤ የፍትህና የእውነተኛ ዴሞክራሲ ጥያቄ ይበልጥ ያስተሳስረናል እንጂ አይበትነንም።እርስ በርሳችን ተደጋግፈን እንድቆም ምክንያት ይሆነናል እንጂ የሶማሊያ እጣ ፈንታ እንዲደርስብን አያደርግም። ኢትዮጵያችን እንደ ሶማሌ አትበታተንም። መለስ ሆይ ሟርትህና ተንኮልህ እንደማይሰምርልህ ተረድተህ ከህዝባችን ጫንቃ ላይ እንድትወርድ እንጠይቅሃለን።

ኢትዮጵያ የወላድ መካን አይደለችም። ኢትዮጵያ አርቆ ማየት የሚችሉ አስተዋይ ዜጎች ያሏት አገር ነች። ኢትዮጵያ እንደ ሶማሊያ እንዳትሆን ለመታደግ ቆርጠው ግዜውን የሚጠብቁ ምርጥና በክፉ ቀን የሚነሱ ልጆች አሏት። ምንም እንኳ የእነመለስ ዜናዊ የጥፋት ሰይፍ መመዘዙ ባይቀርም ያንን መክቶ አገሪቷን በሠላምና በህዝቦች ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ለመዘርጋት የተዘጋጀ ኃይል እንዳላት ለማስገንዘብ እንወዳለን። አሁንም ኢትዮጵያን እንደ ሶማሌ ለማድረግ ቆርጣችሁ የቆማችሁ ግለሰቦች (በተለይም መለስ ዜናዊ) ቆማችሁ ራሳችሁን እንድትመረምሩ እናሳስባችኋለን። በታሪክ ተወቃሾች፤ በህግ ፊት ተጠያቂዎች መሆናችሁንም መዘንጋት አይገባችሁም።

የተከበራችሁ የአገራችን ዜጎች የሁላችንም ጠላት መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ የወለዱት የነጻነት እጦትና የፍትህ መጓደል ነው። ነጻነታችን ተረጋግጦና ፍትህ ነግሶ እስከምናይ ድረስ ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል። የመለስ ዜናዊ ስሜት ህግ መሆኑ ሳያበቃ እንቅልፍ በዓይናችን ዝር አይበል። እኛ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ አባላት በአገራችን ዜጎች ላይ የሚቀልደውን መለስ ዜንዊን ከስልጣን ሳንወርድ አናርፍም። ረፍታችን የመለስ ከስልጣን መባረርና በአገራችን ውስጥ ነጻነት፤ ፍትህና እኩልነት መስፈኑ ነው።እስከዚያ የማንፈነቅለው ድንጋይ የለም።

የመለስ ዜናዊ ስሜት ህግ በሆነበት አገር ዜጎች በሰላም አይኖሩም።የመለስ ዜናዊ ስሜት ህግ በሆነበት አገር ዜጎች ሠርተው ለመኖር የህግ ዋስትና የላቸውም። የመለስ ዜናዊ ስሜት ህግ በሆነበት አገር ዜጎች በእኩልነት እየኖሩ አይደለም። ጥቂቱ በፎቅ ላይ ፎቅ ሲሰራ፤ አይቶት የማያውቀውን ባለቀለም መጠጥ እንደውሃ ሲራጭና ሆዱ ከሚችለው በላይ ያገኘውን ሁሉ ሲያገበስብስ ሌላው በዝምታ የዚህ ሁሉ ተውኔት ተመልካች በሆነበት አገር ውስጥ ሠላም አለ ማለት ራስን ከማታለል የዘለለ ትርጉም ያለው ነገር አይደለም። ኢትዮጵያችን ውስጥ ያለው ዝምታ ሠላም ሳይሆን በቃላት ሊገለጽ የማይችል ሮሮ መሆኑን ለመለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

በተለያየ መንገድ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በሊቢያ ወጣቶች መኩራታችሁን መግለጻችሁን እያየንና እየሰማን ነው። ይሄ መልካም ነገር ነው።ከሊቢያ ወጣቶች ቀደም ብለው የኢትዮጵያ ወጣቶች እምቢ ለነጻነቴ እምቢ ለክብሬ ብለው አገራቸውን በነጻነት ጠብቀው አልፈዋል። አሁን ያሉት የኢትዮጵያ ወጣቶችም ከቀደሙት ዜጎች የወረሱት የነጻነት መንፈስ በውስጣችሁ እነደሚነድ እናውቃለን። ኢትዮጵያችን ለነጻነቱ ቀናዒና ለክብሩ ሟች ትውልድ ባለቤት ነች።በላይ ዘለቀ፤ አብዲሳ አጋና ሌሎችንም ያፈራች አገር ነች።በላይ ዘለቀና አብዲሳ አጋ የነበራቸው ሃሞት የዛሬውም ወጣት አለው።የበላይና የአብዲሳ የጀግንነት መንፈስ በዛሬው ትውልድ ላይም አለ። የዘመኑም ትውልድ ነጻነቱን የሚጠይቅበት ግዜ ሩቅ አይደለም። ብዝበዛ፤ ዘረኝነት፤ ጭቆናና በስልጣን መባለግ ይብቃ የሚልበት ግዜ እየመጣ ነው።

ውድ የተከበራችሁ

የአገራችን ዜጎች ለነጻነት የሚደረግ ትግል አርቆ አስተዋይነትን፤ርህራሄንና ፍቅርን ይጠይቃል። እነመለስ ዜናዊ በብሄራችንና በሃይማኖታችን ከፋፍለው እርስ በርሳችን እንድንጫረስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ማወቅ ይኖርብናል። ለነመለስ ዜናዊ የሰው ልጆች ህይወት የቁጥር ጨዋታ እንጂ ሌላ አይደለም። ስንት በመቶ የሚሆነውን ለእርድ እናቅርብ ብለው ያሰላሉ እንጂ የሰው ልጆች ደም መፍሰስ ቅንጣት ታክል የሚቆጫቸው ሰዎች አይደሉም።ለነጻነቱ የሚታገል ሰው በአንድ ብሄር ላይ ካነጣጠረ ጥላቻ ራሱን ማራቅ አለበት። ጠላታችን አንድ ብሄር ወይም የአንድ ወገን ህዝብ አይደለም።ችግራችን የነጻነት ማጣትና የፍትህ መጓደል ነው።የምናተኩረውም ነጻነታችንን ነጥቀው በሚያዋርዱን ሃይሎች ላይ ነው እንጂ ሌላ ማንም ላይ አይደለም።

በየትኛውም ዓለም ህዝብ የህዝብ ጠላት ሁኖ አያውቅም።እነመለስ ዜናዊ ግን አንድ ህዝብ የሌላው ህዝብ ጠላት እንደሆነ ሲሰብኩ ኖረዋል።የሰማቸው ግን አልተገኘም። ይህን ክፉ ምኞታቸውን በተግባር ለማሳየት ግን የሚችሉትን ሁሉ ሞክረዋል ወደፊትም እንደሚሞክሩ መጠበቅ አለብን። ስለሆነም የነመለስ ዜናዊን የተንኮል ወጥመድን ሰብሮ ለማለፍ ሁላችንም በፍቅር፤በአንድነትና በጽናት እንድንታገል ግዜውና ሁኔታው ግድ ይለናል። ድምጻችንንም ከፍ አድርገን ኢትዮጵያ ሶማሊያንን እንደማትሆን ለመለስና ለግብረ አበሮቹ ማሳሰብ አለብን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የግንቦት7 አላማ ምንነት፤ ለምንና እንዴት በሚል ርዕስ ከታተመው የግንቦት7 መጽሃፍ የተወሰደ ( ክፍል 4 የመጨረሻ ክፍል )

### የፖለቲካ ነጻነት

‹‹የፖለቲካ ነፃነት›› የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ልንተረጉመው እንችላለን፡፡

1. የተሟላ የፖለቲካ ነፃነት መኖር በግለሰብ ሉዓላዊነት ላይ የጉልበት ጣልቃ-ገብነት አለመኖር ማለት ነው፡፡ የግለሰብ ሉዓላዊነት ደግሞ አንድ ሰው ችሎታውን ተጠቅሞ ፍላጎቶቹን የማሟላት ተፈጥሮአዊ መብት ነው፡፡ እናም የፖለቲካ ነፃነት መኖር ይህ መብት በሰው ወይም ሰው በፈጠረው ተቋም አለመገደቡን ያመለክታል፡፡
2. የፖለቲካ ነፃነት ማለት አንድ ግለሰብ ተፈጥሮአዊ ችሎታውን ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞ ፍላጎቶቹን ለማሟላት የሚያስፈልገው ኃይል እና/ወይም ሥልጣን እና/ወይም ግብዓቶች ተሟልተውለታል ማለት ነው፡፡

የመጀመሪያው ትርጉም ግለሰብ ሰው በመሆኑ በተፈጥሮ የተጎናፀፈውን ፀጋ በተግባር ላይ ለማዋል የሚያደርገውን ጥረት በጉልበት የሚገታው አለመኖሩን ሲገልፅ (negative liberty)፤ ሁለተኛው ደግሞ ሰው የመሆንን ፀጋ ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ላይ (positive liberty) ያተኩራል:: የመጀመሪያው ትርጓሜ ግለሰብ በተናጠል ሁለተኛው ደግሞ ግለሰብን በማኅብረሰብ ውስጥ የሚያዩ በመሆናቸው በሁለቱ መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም ሁለቱም ትርጓሜዎች በነፃ ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች በግልም ሆነ በጋራ ያሏቸውን ያልተገደቡ ሰፊ መብቶችን ይመለከታሉ፡፡

የፖለቲካ ነፃነት መሰረቱ የሰው በሰው መጨቆን፣ መገዛት፣ መገደድ አለመኖርን ነው፡፡ የፖለቲካ ነፃነትን በተሟላ ሁኔታ ለመጠቀም ደግሞ የመኖርን፣ የመማርን፣ በነፃነት የማሰብን የመሳሰሉ መሰረታዊ መብቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ የፖለቲካ ነፃነት እጦት የሚፈጠረው በአብዛኛው ሥልጣን በጥቂቶች እጅ በገባ ጊዜ ነው ፡፡ ስለሆነም ለፖለቲካ ነፃነት አስፈላጊ ከሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች አንዱና ዋነኛው ሥልጣን በጥቂት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እጅ እንዳይገባ ማድረግ ነው፡፡ የፖለቲካ ነፃነት አይነቶች ብዙዎች ቢሆኑም የሚከተሉትን ለአብነት መግለፅ ይበቃል፡፡

- የመሰብሰብ ነፃነት፣
- የመደራጀት ነፃነት
- የመማር ነፃነት
- ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ነፃነት
- የእምነት ነፃነት
- የመናገር ነፃነት
- የፕሬስ ነፃነት
- የሃሳብ ነፃነት
- የአካዳሚ ነፃነት
- የፆታ ነፃነት
- ራስን የመከላከል ነፃነት
- መሪዎችን የመምረጥ ነፃነት

የፖለቲካ ነፃነትና ማኅበራዊ እድገት በበርካታ መንገዶች የተያያዙ ናቸው፡፡ ነፃነት ዜጎች በተፈጥሮ ያገኙትን እና/ወይም በትምህርትና ልምድ ያካበቱትን ችሎታ ፍላጎታቸውን በሚያረካ መንገድ የመጠቀም እድላቸውን ስለሚያሰፋ ምርምርንና ፈጠራን ያዳብራል፡፡ ነፃነት የሰው ልጅን ምኞቶች ያሳድጋል፡፡ የፍላጎቶች ማደግ ደግሞ አዕምሮን ለማሰብ፣ ለመመራመርና ለፈጠራ ያመቻቻል፡፡ ለነፃ ማኅበረሰብ ማበብ ችግርና ያልተሟሉ ምኞቶች የስኬት ምንጮች ናቸው፡፡ በመሆኑም የነፃነት መኖር ዘላቂ ለሆነ እድገት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እድገት ያለ ነፃነት ትርጉሙ አነስተኛ ነው፡፡ በቁሳዊ ምቾት ቢንበሸበሽም፣ ሰው ሰብዓዊ ክብሩን ከተነፈገ፣ ይዋል ይደር እንጂ ራሱን ጌቶቹ ከሱ ምን እንደሚፈልጉ ሳያውቅ በመድለብ ላይ እንዳለ ፍሪዳ አድርጎ መቁጠሩ የማይቀር ነው፡፡

ሰውን ቁሳዊ ምቾት ብቻ አያኖረውም። ማኅበራዊና መንፈሳዊ ምቾቶችንም ይፈልጋል፡፡ እንዲያውም የሰው ልጅ ራሱን ባበቃ (ማለትም ባሳደገ) መጠን ለማኅበራዊና መንፈሳዊ ምቾቶች ያለው ክብር እየበዛ፤ ለቁሳዊ ምቾቶች ያለው ክብር ደግሞ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ታላላቅ መሪዎች ለክብራቸው፣ ለዓላማቸው፣ ለድርጅታቸው ሲሉ መራብን፣ መጠማትና መሰቃየትን ብቻ ሳይሆን መሞትንም በደስታ የሚቀበሉት።

### ማጠቃለያ

ከእዚህ በላይ በስፋት የቀረበው ጽሁፍ በአጭሩ መጨመቅ ይቻላል፡፡ የነጻነት ጉዳይ ሰው የሚደርግን ከሌለው ሁሉ ፍጥረት የሚለየን ወደ እዚህ ምድር ስንመጣ አብሮን የመጣ የተፈጥሮአችን አካል ነው፡፡ ይህንን ነጻነት ከሰው መግፈፍ አይቻልም፡፡ ሰው ነጻ መሆኑን ማስቆም የሚቻለው አንድም ሰውየውን በመግደል ወይም ኮማ ውስጥ በመጨመር ብቻ ነው፡፡ የሰው ልጅ ነጻነት በማህበረሰብ ከመደራጀቱ አስቀድሞ በሰውነቱ የመጣ ነጻነት ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮ ነጻነት ገደብ የሌለው በስፋቱ ታላቅነት በውቅያኖስ ላይ ለብቻው እንደተጣለ ሰው ባለቤቱን የሚያሸብር ነው፡፡

በማህበረሰብ ውስጥ በፖለቲካ በኢኮኖሚ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎቻችን ላይ የምንጥላቸው የነጻነት ገደቦች ሁላችንም በተናጠል በተፈጥሮ ባገኘነው ነጻነት እንጓዝ ብንል የሚከተለውን ቀውስ ለመከላከል ነው፡፡ እነዚህ ገደቦች ደግሞ ሁላችንም በስምምነት የደረስንባቸው ውሎች ውጤቶች መሆናቸው ከሰብአዊ ክብራችን ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ እኛ ያልተስማማንበትን የነጻነት ገደብ ላድርግባችሁ የሚል አምባገነን ከመጣ የማይዋጥልንም ለእዚሁ ነው፡፡ ዛሬ በሃገራችን የሚካሄደውን የነጻነት ትግል ልዩ የሚያደርገው የኢትዮጵያ ህዝብ የእዚህ አይነቱ ነጻነት ባለቤት መሆኑን የተረዳበት፣ በላዩ ላይ የተዘፈዘፉ ዘረኞችና አምባገነኖች እንደ ከዚህ ቀደሙ ገዥዎች ከሰማይ የወረዱና ምንም ሊያደርጋቸው የማይችል አድርጎ የማያይበት ምእራፍ ላይ የደረሰበት መሆኑ ነው፡፡

ይህ አዲሱ የነጻነት እይታ የሚያስጨንቅ ነው እናዳልነው ሁሉ የሚያስደስትም ነው። የመከራችንና የዘረኛ አምባገነኖች ቀን ማጠሪያ መቃረቡን የሚያመላከት ነውና፡፡ ሌላ ዙር የባርነት ሥርዓት በሃገራችን ሊመጣ የማይችል መሆኑን የሚጠቁም ነውና፡፡

እያንዳንዱ የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አባል ነፃነት ሰው የመሆናችን መታወቂያችን መሆኑን በመረዳት ከነፃነቱ የሚያስበልጠው ምንም ነገር የለም ተብሎ ይታመናል:: የግንቦት 7 አበላትን የዚሁ የነጻነት ትግል ግንባር ቀደም ታጋዮች የሚያደርገን ይህ እውነታ ነው፡፡ በቃላችንና በተግባራችን የነጻነት ሃዋርያት ሆነን በመገኘት በቅድሚያ እራሳችንን ነጻ አውጥተን ሌላው ወገናችን ለነጻነቱ የሚያደርገውን ትግል በመደገፍ ከጎኑ መቆም እንችላለን፡፡

## ዊኪ ሊክስ እጅግ በርካታ የሚስጥራዊ መረጃ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሰነዶቹን በትኩረት የማጥናት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ከገለጹልን በሁአላ መረጃዎችን ሙሉ በሙሉ ማንበብ፤ አንብቦም መረዳት እና ለትግላችን ያላቸውን እንድምታ ለመመዘን ጊዜ የሚፈጅ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በሰነዶቹ ላይ የሚኖረንን አስተያየትም ሆነ ለትግላችን የሚሰጠውን ጠቀሜታ ወደፊት የምንገልጸው ይሆናልይሁን እንጂ የተለቀቁትን መረጃዎች በጥሬው ስንመለከት የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ አምባገነንነቱ እየጨመረ የመጣ መሆኑን፣ በእስረኞች ላይ አስቃቂ ሰቆቃዎችን (ቶርቸር) የሚፈጽም መሆኑን፣ የመለስ አገዛዝ የሚደሰኩረው የኢኮኖሚ እድገት ውሸት መሆኑን፤ ከመለስ ዜናዊ የቅርብ ባለሚሎች እንኳን ሳይቀር በሥርዓቱ የተማረሩ እና ተስፋ የቆረጡ መኖራቸውን አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በደንብ ያውቃል፤ ይህንኑም ዋሽንግተን ለሚገኘው የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አሳውቋል ብለዋል።

በተያያዘ ዜና በህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ምርጫ ወቅት መለስ ዜናዊ በአርከበ እቁባይ ተሸንፎ እንደነበር ዊኪሊክስ ይፋ ካደረገው ምስጥራዊ መረጃ ለማወቅ ተችሎአል።

በዊክሊኪስ ይፋ በሆነው የአሜሪካ ኢምባሲ ሚስጢራዊ መልእክት ዉስጥ እንዳተመለከተው፤ የህወሀት የአመራር አባላት በሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ምርጫ ወቅት፣ አርከበ እቁባይን በአንደኝነት፣ ዘረኛውን መለስ ዜናዊን በሁለተኛነትና ስዩም መስፍንን በሶስተኛነት እንደተመረጡ የነበር ሲሆን። ይሁን እንጅ አርከበ እቁባይ የፓርቲው ሊቀመንበር ወይም ምክትል ሊቀመንበር እንዲሆን በፓርቲው አባላት ቢጠየቅም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርትዋል። እርከበ ስልጣን ለመረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው በመለስ ዙሪያ የተሰባሰቡትን ሰዎች በመፍራት ነውም ተብሎአል።

የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የስትራቴጂክ እቅድ አማካሪ የሆኑትን እንግሊዛዊውን ጸሀፊና ጋዜጠኛ ፓትሪክ ጊልክስን በመረጃነት የሚጠቅሰው የኢምባሲው መረጃ እንዳመለከተው መለስ የህወሀት አባላትን ድምጽ ያጣበት ዋና ምክንያት በባድሜ ጦርነት ምክንያትና በአገሪቱ የሚታየው የኢኮኖሚ ቀውስ የትግራይን ህዝብ እየጎዳ መሆኑ ስለታመነበት ነው።"

በብአዴን፣ በኦህዴድ፣ በደህዴን እና በሶህዴፓ ውስጥም ተመሳሳይ ክፍፍል ተፈጥሮ እንደነበር ይፋ ያደረገው ምስጥራዊዉ መረጃ በመቀጠልም ተፈራ ዋልዋ የህወሀትን የበላይነትና ለረጅም ጊዜ በስልጣን መቆየትን ከሚቃወሙት ውስጥ የተፈረጀ ሲሆን፣ በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ ደግሞ የህወሀት የበላይነት እንደተጠበቀ እንዲቆይ ፍላጎት ነበራቸውም ተብሎአል።

እነ በረከትና አዲሱ፤ ተፈራ ዋልዋን ከብአዴን ምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ ያነሱበት ምክንያትም ተፈራ የህወሀትን ፍጹም የበላይነት እየተቃወመ በመምጣቱ መሆኑ ተመልክቶአል።

በተመሳሳይም አቶ ስዩ አብረሀን በዋቢነት የጠቀሰው የአሜሪካ መረጃ እንደሚያመለክተው ለሱዳን የተሰጠው ሰፊ የአማራ ክልል መሬት በብአዴኖች መካከል ልዩነት እንዲፈጠር አድርጓል። አምባሳደር ዶናል ያማማቶ በላኩት መልክት ህወሃት ውስጥ ከ10 አመት በፊት ተከስቶ በነበረው ክፍፍል ምክንያት መለስ ዜናዊ ስልጣኑን ሊያጣ ተቃርቦ እንደነበርና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት ትችቶችንና አስተያየቶችን በቀናነት እንደማያይ ገልጸዋል።

ህዝብን በመሳሪያ ሃይል አንቀጥቅጦ እስከወዲያኛው የመግዛት ዕቅዱ እንደማይሳካ እየተረዳ የመጣው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰሜን ጎንደር የህዝቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በጥብቅ ከመከታተል አልፎ ባልተጠበቀ ሰዓት በሠላማዊ ዜጎች ቤት ዘው ብሎ በመግባት የመሳሪያ ፍትሻ ማካሄድ እንደጀመረ ዘጋቢያችን ከስፍራው በላከልን ዜና ገለጸ።

## የዘረኛው አገዛዝ በትር ታማኝ አገልጋዮቹንም እየገረፈ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን በባለስልጣናቱ ላይ ይህ ርምጃ የተወሰደበት ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲገልጹለት በክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ በኤክስፐርትነት በማገልገል ላይ የሚገኙ ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈቀዱ ባለሙያን በስልክ አነጋግሮ ባገኘው ምላሽ፤ በይፋ እየተነገረ ያለው በክልሉ ላይ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር እጦት እየተንሰራፋና ከፍተኛ ሙስና እየተፈጸመ በመምጣቱ ነው የሚል ሲሆን፣ ነገር ግን ስለመልካም አስተዳደር እጦትና ስለሙስና ካወራን የአሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ እንደሚባለው የሃገሪቱን ስልጣን ተቆጣጥረው የሚገኙት ባለስልጣናት በሙስናም ሆነ መልካም አስተዳደርን ባለማስፈን ቀዳሚውን ስፍራ በያዙና ርምጃውም በነሱ በጀመረ ነበር ይሁን እንጂ ወያኔ ባሁኑ ሰአት የተያያዘው ስልት፣ በጥርጣሬ አይን የሚያያቸውን፣ ዘረኛነትን መሰረት ላደረገ አሰራሩ አመቺ ሆነው ያላገኛቸውን ባለስልጣናት ሰበብ አስባብ በመፈለግ ማባረር ነው። እናም ያሁኑ ርምጃ ምንም የሚያስገርም አይደለም፣ ወይንም የሚያሳዝንም አይደለም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተግባራዊ እየሆነ የመጣ የተለመደ አሰራር ነው ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች ለአገዛዙ ታማኝና ታዛዥ ናቸው የሚባሉ ሆድ አደሮችን ወይንም የስልጣን ሱሰኞችን ወደ ከፍተኛ ስልጣን በማምጣት፣ እንደፈለገው ሲያሽከረክር ይቆይና፣ አልመች ባሉት ጊዜ ከስልጣን እንደሚያባርርና ወደ እስር ቤቶችም እየወሰደ እንደሚያጉራቸው በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን ይታወሳል።

## ዘረኛው አገዛዝ ታማኝና አገልጋዮቹ ናቸው ብሎ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሌላም በኩል በሃገሪቱ የሚገኙ አብዛኞቹ የንግዱ ማህበረሰብ አካላት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እየጣለባቸው ያለው ኢ ፍትሃዊ የግብር እዳ እጅግ እያስመረራቸው መሆኑን በዚህም ምክንያት ከአብዛኞቹ የንግዱ ማህበረሰብ አካላት የወያኔው አገዛዝ በነጋዴዎች ላይ ጦርነት አውጇአል፣ በመሆኑም ነጋዴው የቱኒዝያና የግብጽ አይነት ንቅናቄ ካላሳየ በስተቀር፤ ባለፈው የዋጋ ተመን ላይ እንደተደረገው ነጋዴውን የማሰቃየት የረቀቀ ድርጊት፤ በተፋፋመ መልኩ መቀጠሉ አይቀሬ ነው በማለት በግልጽ እየተናገሩ መሆኑን ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ፤ላይ አመልክቱአል።

ዘጋቢያችን የዘረኛው አገዛዝ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ እየፈጸመ ያለውን በደል አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከሚገኙ የንግዱ ማህበረሰብ አካላት ውስጥ ያነጋገራቸው ግለሰቦች በሰጡት አስተያየት፤ የወያኔ አገዛዝ ባለፈው አንድና ሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ40% በላይ ተጨማሪ ገንዘብ ያተመ፣ ባለፉት ሁለት አመታት ጊዜ ውስጥ የብርን የመግዛት አቅም 50 % ያዳከመ፣ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥን በማወሳሰብ እና መጠይቅን በማብዛት ነጋዴውን እያዳከመ ያለ፣ የተጋነነ ዋጋ ከደረሰኘ ውጭ በመተመን ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች ላይ፣ የውሸት ህግን ተገን ያደረገ ዘረፋ እያካሄደ ያለ፣ ያልሰሩትን ሰርተዋል በማለት፤ ነጋዴዎችን በግብር ከንግድ ውጭ እያደረገ ያለ፣ እንደ ቡና፣ የምግብ ዘይት የመሳሰሉት የምግብ ፍጆታዎችን በተለያየ ሰበብ ለራሱ ወይም ለአገዛዙ ቅርበት ላላቸው ድርጅቶች እያስተላለፈ ያለ፣ እንዲሁም ከግል ባንኮች ላይ በብድር ዘረፋን እያኪያሄደ ያለ አገዛዝ ነው። በመሆኑም እኛ ነጋዴዎች ህልውናችን ይጠበቅ ዘንድ ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ መነሳት ያለብን አሁን ነው በማለት ገልጸዋል።

ከዚሁ ዘገባ ጋር ተያይዞ የመቀሌ ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ ማውጣት አልቻልንም በማለት እያማረሩ መሆኑን ባንጻሩ ደግሞ የዘረኛው አገዛዝ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ግብር መክፈል እያለባቸው ያልከፈሉ፣ ወደ ታክስ ሥርዓቱ ያልገቡ ‹‹ሕገወጦች›› በሚላቸው ነጋዴዎች ላይ ዕርምጃ ሊወስድ ዝግጅት ያደረገ መሆኑን ማስታወቁን ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ዘገባ ገልጹአል እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የመቀሌ ከተማ ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ ለማውጣት ወደሚመለከተው አካል ቢሄዱም፣ ፈቃድ መስጠት በመቆሙና መቼ እንደሚጀመር ባለመገለጹ ችግር ገጥሞናል ማለታቸውንና ፈቃድ መስጠቱ ግልጽ ባለመሆኑ ምክንያት መቋረጡ ብቻ ሳይሆን፣ የንግድ ፈቃድ ለማደስም ለሁለት ወራት እንዲጠብቁ መደረጉ በንግድ ሥራቸው ላይ ጉዳት ማድረሱን ሪፖርተር በመባል የሚታወቀው ለአገዛዙ ቅርበት ያለው ጋዜጣ መዘገቡንም አክሎ ገልጹአል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በጅምላ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመድረክ አባላት የሆኑና በኦሮሚያ ክልል በስፋት የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች አመራሮችንና አባላትን በገፍ በማሰር ላይ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ላይ ደግሞ በደህንነትና በፖሊስ ግልጽ ክትትል እያስፈራሯቸው መሁኑን ምንጮች አስታወቁ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ኢሳት እስካሁን ከ50 በላይ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) እና የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግረንስ (ኦህኮ) ፓርቲዎች አመራሮችና አባላት በፌዴራል ማዕከላዊ ቢሮ ከየቤታቸውና ከየሥራ ገበታቸው ያለፍድ ቤት ትዕዛዝ ተይዘው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ከሁለቱ ፓርቲዎች ያገኘውን መረጃ ዋቢ በማድረግ ዘግቦአል።

የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ባለፈው ዕሁድ በሰጠው መግለጫ በመድረክ ሥር የተሰባሰቡ 29 የኦፌዴንና የኦህኮ ፓርቲዎች አባላትን በሽብርተኝነት ተግባር ሲንቀሳቀሱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር አውያቸው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ አድርጌያለሁ ብሏል፡፡

የኦህኮ ፓርቲ ኃላፊ የሆኑት አቶ አልባና ሌሊሳ ቅዳሜ ነሐሴ 21 ቀን 2003 ዓ.ም እንደወትሮው ስድስት ኪሎ አፍንጮ በር አካባቢ በሚገኘው በመድረክ ጽ/ቤት የፓርቲ ሥራቸውን እስከ ቀኑ 6፡30 ሲያከናውኑ ቆይተው ከቢሮ አቅራቢያቸው በሚገኘው ሱቅ ዕቃ በመግዛት ላይ ሳሉ በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ በቁጥጥር ሥር ውለው መጀመሪያ ወደ ቅድስተማሪያም አካባቢ ከተወሰዱ በኋላ 40 ደረጃ አቅራቢያ ወደ ሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ተወስደው ቤታቸው እንደተበረበረና ወደ ማዕከላዊ እሥር ቤት ተወስደው እንደታሰሩ የመድረክ የሥራ ባልደረባቸው አቶ አለሙ ኮየራ ለኢሳት ሪፖርተር መናገራቸው ተዘግቦአል፡፡

የኢሳት ሪፖርተር ያነጋገራቸው የአቶ አልባና ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ የማታወርቅ መንገሻ በበኩላቸው ”ባለቤቴን ሊያሳስር የሚችል አንዳች ምክንያት ካለ ያው በሕጋዊ መንገድ በተቃዋሚ ፓርቲ እንቅስቃሴ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት መንቀሳቀሱና መሳተፉ ነው” ያሉ ሲሆን እርሱ በቁጥጥር ሥር ሲውል እኔ ኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ የሥራ ገበታዬ ላይ ስለነበርኩ ቤቴን ሲበረብሩ ስላልነበርኩ ምን ዕቃ እና ዶኩመንት እንደወሰዱ እስካሁን አላወቅሁም ነገር ግን ማታ ቤቴ ስገባ እኔ ባለቤቴ አልባና እና አንድ የእርሱ ዘመድ በኦሮሞ የቦረና አባ ገዳ ባህላዊ አለባበስ የተነሳነውን የፎቶ ፍሬም ለምን እንደ ወሰዱት ግን አልገባኝም ማለታቸውን አስታውቆአል፡፡

የኦፌዴን ፓርቲ ዋና ጸሐፊ የሆኑት አቶ በቀለ ነጋ ኢህአዴግ ሀገሪቷን እንደ ግል እርስት ይዞ እንደፈለገው እያደረገ ሲሆን በተለይ ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብና ለሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ኢሰብዓዊ ድርጊቱን የሚያጋልጡበትን ግለሰቦች፣ ጋዜጠኞችና ፓርቲዎች ሆን ብሎ ለማጥፋት አበክሮ እየሰራ ነው ማለታቸውን የኢሳት ዘገባ አመልክቶአል፡፡

አቶ በቀለ «የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲው ዛሬ ኦሮሞ ላይ ዘምቷል፣ ነገ ደግሞ ሌላው ላይ መዝመቱ አይቀርም፣ ይህ ገዢው ፓርቲ ወደ አንድ ወጥ የአንድ ሰው አምባገነንነት መለወጡን የሚያሳይ ሲሆን ዛሬ ለአንተ በቢሮዬ በሰጠሁት መረጃ እኔም አሸባሪ ተብዬ ነገ ስላለመያዜ ምንም ማስተማመኛ የለኝም» ማለታቸውንም ኢሳት ዘግቦአል።

ሲፒጄ በመባል የሚታወቀው የጋዜጠኞች ጥበቃ ተቋዋም “ሽብርተኞች” ናችሁ ተብለው የታሰሩት የሁለት ጋዜጠኞች ጉዳይ እጅግ ያሳሰበው መሆኑን በመግለጽ መግለጫ ማውጣቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ሂዩማን ራይትስ ዋች በበኩሉ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና አባላት ከዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እስራት ነጻ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርቡአል። በተመሳሳይ መልኩ አዲስ ነገር ኦን ላይን በመባል የሚታወቀው የመረጃ ድረ ገጽ ባወጣው ዘገባ የወርሐዊው “የሙስሊሞች ጉዳይ” መጽሔት አዘጋጅ የሱፍ ጌታቸው አደገኛ ማስፈራሪያ እንደደረሰው ሰሞኑን ለፍትሕ ጋዜጣ መናገሩም ታውቁአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም በኢትዮጵያ ህዝባዊ አመጽ ይነሳል የሚል ፍራቻ ካደረበት ወዲህ ኢትዮጵያዊያንን ለማሸማቀቅና ለማስፈራራት ኢፍትሃዊ የሆነ እስራትና ሰቆቃ በዜጎች ላይ እየፈጸመ መሆኑን በስፋትና በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ:-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ:-** በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz

እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org